# ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ



ሃዋሳ አረጋዊያን ማዕከል

2013/2014
የበጀት ዓመት ሪፖርት

መጋቢት 2014
አዲስ አበባ/ኢትዮጵያ

# ልዩ ምስጋና

## “የተቻለውንና ያለውን መስጠት ታላቅነት ነው”







- ስም፡ ደራሲ.ሜሪ ጃፋር
- አድራሻ፡አዲስ አበባ
- የሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ የረጅም ዓመት በጎ ፈቃደኛ

ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ በሚያካሂደው የመንግስት-ማህበረሰብ-የግሉ ሴክተር አጋርነት “ኢትዮጵያዊያን ለኢትዮጵያዊያን” ፕሮግራም ድጋፍ ለሚሹ አረጋውያን እና ህፃናት ሀብት ለማሰባሰብ የሚደረገውን ጥረት በሙያቸው፤ በእውቀታቸው እንዲሁም ባላቸው አቅም የላቀ አስተዋፅኦ ካደረጉ የረጅም ዓመታት ግንባር ቀደም በጎ ፍቃደኞች መካከል ደራሲ. ሜሪ ጃፋር አንዷ ናት፡፡ እርሷ ለሰው ልጆች ያላትን የውስጥ ስሜት፤ ርህራሄና ተቆርቋሪነት በቃል ከመግለጽ ይልቅ በጽሑፍ እና በግጥም መግለጽ የሚቀላት እንቁ ኢትዩጵያዊ ነች፡፡ ደራሲ. ሜሪ ጃፋር ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ለህፃናት እና አረጋዊያን ድጋፍ በሚያዘጋጃቸው መርሐግብሮች ሁሉ ቀድማ የምትገኝ፤ ለስኬታማነቱ የምትችለውን ያለ ስስት የምታደርግ፤ የምታስተባብር በመሆኗ ታላቅ ክብርና አድናቆት የሚገባት ነች፡፡ ለምሳሌ የሃዋሳ አረጋዊያን ማዕከል እንዲገነባ፤ ለአርባምንጭ እና ሆሳዕና አረጋዊያን ማዕከላት ግንባታ የሃብት ማሰባሰብ ስራ ላይ ተሳትፋለች፤ በዓላትን እና አዲስ ዓመትን ምክንያት በማድረግ ከተለያዩ በጎ ፍቃደኛ አርቲስቶች እና በጎ ፈቃደኞች ጋር በመሆን ከወርቀ ዘቦ መልቲሚዲያና ኮሚኒኬሽን ጋር በመተባበር የተዘጋጀው አረጋውያንን እና ህፃናትን የገና በዓል ምገባ ፕሮግራም ጥሩ በዓል እንዲያሳልፉ ትልቅ ስራ ሰርታለች፡፡

ደራሲ. ሜሪ ጃፋር ከላይ የተጠቀሰውን በማድረጓ አረካችም ይልቁንም የሰው ልጅ የተቻለውን እና ያለውን ሲሰጥ ይህ ታላቅነት ነው እንደሚባለው ከ150 ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ከቤተሰቦቿ የተሰጣትን አሁን ባለው ዋጋ ግምቱ 189,000.00 **ብር** የሚያወጣ 21 ካራት 42 ግራም ወርቅ እረዳት ለሌላቸው ህፃናትና አረጋዊያን ድጋፍ እንዲውል ለግሳለች፡፡ በአጠቃላይ ይህች ደግ ኢትዮጵያዊት ላደረገችው በጎ ሥራ የተሰማንን በቃላት መግለጽ የሚከብደን ሲሆን ለሌሎችም ትልቅ አርአያነት ያለው በመሆኑ በሕጻናቱ እና አረጋዊያኑ ስም መላው የሜሪ ጆይ ቤተሰብ ከልብ እናመሰግናለን፡፡



## ራዕይ

ሜሪ ጆይ በተጠቃሚዎች ሕይወት ላይ የዘለቄታ መሻሻልን የሚያመጣ ቀጣይነት ያለው ድርጅት ለመሆን ይሰራል



## ተልዕኮ

የሜሪ ጆይ ተልዕኮ የተቀናጀ የልማት ስራ በማከናወን ለችግር ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ሕይወት መለወጥ ነው



## እሴቶች

ቁርጠኝነት፤ ግልፅነት፤ ተጠያቂነት፤ ተአማኒነት፤ ከወገንተኝነት አድሎአዊ አሰራር ነፃ መሆን

# ማውጫ

i የቦርድ ሰብሳቢ መልዕክት ---------------------------------------------------------------------------------- i

ii. የዋና ስራ አስኪያጅ መልዕክት ----------------------------------------------------------------------------- ii

1. መግቢያ------------------------------------------------------------------------------------------------ 1

2. የተግባራት እና በጀት ዓመታዊ አፈፃፀም --------------------------------------------------------------------- 2

2.1 የኢኮኖሚ አቅም ግንባታ ------------------------------------------------------------------------------ 3

2.2 ትምህርት ------------------------------------------------------------------------------------------ 5

2.3 ጤና ------------------------------------------------------------------------------------------------ 5

2.4 የመንግስት - ማህበረሰብ - የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አጋርነት ----------------------------------------- 9

3. አስተዳደር እና አመራር ----------------------------------------------------------------------------- 16

4. የፋይናንስ አፈፃፀም --------------------------------------------------------------------------------- 16

4.1 የገቢ ትንተና -------------------------------------------------------------------------------------- 16

4.2 የወጪ ዝርዝር ------------------------------------------------------------------------------------17

5. የሰው ኃይል አፈፃፀም ------------------------------------------------------------------------------ 18

5.1 የሰው ኃይል አጠቃቀም ---------------------------------------------------------------------------- 18

5.2 የሰራተኞች አቅም ግንባታ አፈፃፀም -------------------------------------------------------------- 18

6. የድርጅቱን ዘላቂነትና የሀብት መሰረት ማጠናከር --------------------------------------------------- 19

6.1 የገቢ ማስገኛ (አይጂኤ) ----------------------------------------------------------------------------19

7. ክትትል እና ድጋፍ፤ መረጃ አደረጃጀት -----------------------------------------------------------------19

8. ሌሎች ዋና ዋና ክንውኖች -------------------------------------------------------------------------- 20

8.1 የድርጅቱ መዋቅራዊ ማሻሻያ እና የአሰራር ስርዓትን ማጠናከር ---------------------------------- 20

9. የ2014/2015 ዓመት በጀት እቅድ ----------------------------------------------------------------------21

10. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች ------------------------------------------------------- 23

10.1 ያጋጠሙ ችግሮች --------------------------------------------------------------------------------- 23

10.2 መፍትሄዎች ------------------------------------------------------------------------------------- 24

11. ምስጋና ------------------------------------------------------------------------------------------- 24

12. የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት------------------------------------------------------------------------------

13. አባሪ ----------------------------------------------------------------------------------------------- 25

## ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ የሚሰራባቸው አካባቢዎች

| ክልል/ ከተማ አስተዳደር | ዞን /ክፍለ ከተማ | ወረዳ /ከተማ |
|---|---|---|
| ደ/ብ/ብ/ህ/ክልል | ጌዲዮ | ዲላ |
| | ሃዲያ | ሆሳዕና |
| | ወላይታ | ሶዶ |
| | ጋሞ | አርባምንጭ |
| | ጉራጌ | ቡታጂራ |
| | ደቡብ ኦሞ | ጂንካ |
| ደቡብ ምእራብ ክልል | ቤንች ማጂ | ሚዛን አማን |
| | ሸካ | ቴፒ |
| ሲዳማ | | ሃዋሳ ፤ ይርጋለም |
| ኦሮሚያ | ፊንፊኔ ዙሪያ | ቢሾፍቱ |
| አዲስ አበባ | ኮልፌ ቀራንዮ | 11፤12፤13፤ 14፤ 15 |
| | የካ | 01፤02፤03፤04፤05፤08 |
| | ቦሌ | 01፤02፤03 |
| | ጉለሌ | 9፤10 |

## የተከናወኑ ፕሮጀክቶች ዝርዝር

በበጀት ዓመቱ ከለጋሽ ድርጅቶች እና በሀገር ውስጥ ሀብት አሰባሰብ በተገኘ ድጋፍ የተለያዩ ፕሮጀክቶች የተከናወኑ ሲሆን እነሱም ፡-

- ቤተሰብ ተኮር የኤችአይቪ መከላከል፤ድጋፍና ህክምና አገልግሎት - የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ትብብር፤
- የከተማ ልማት ድጋፍ ፕሮግራም የተቀናጀ የአረጋዊያን አገልግሎት - ዓለም ባንክ እና ሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
- የሳንባ ካንሰር መከላከልና ህክምና ማቴዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ
- ከስደት ተመላሽ ህፃናት አቅም ግንባታ እና በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መልሶ ማቋቋም ፕሮግራም- ዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት፤
- የህፃናት እና የአረጋዊያን ስፖንሰርሺፕ፡ የሃዋሳ አረጋዊያን ማዕከል ሁለገብ አገልግሎት- የመንግስት-የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አጋርነት
- የህፃናትና ወጣቶች ማዕከል አገልግሎት- ለጋሽ ድርጅቶችና በማህበረሰቡ፤
- የተቀናጀ የመከላከልና ህክምና አገልግሎት በአዲስ አበባና ሃዋሳ ጤና ማዕከላት (ክሊኒኮች) ናቸው፡፡





በብሔራዊ ቤተመንግሰት - አንድነት ፓርክ
ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው፣ የጠቅላይ ፍርድቤት ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ አቃቤ ህግ እና ሚኒስሮችበስፖንስርሺፕ
ድጋፍ ከሚያደርጉላቸው ህፃናት ጋር የትውውቅ ፕሮግራም




Design by - Assefa Gebeyehu consulting Architects & Engineers.

# የጠቅላላ ጉባኤ አባላት






የቦርድ አባላት በድርጅቱ ዓመታዊ የተግባር እና በጀት አፈፃፀም ላይ ውይይት ሲያደርጉ መጋቢት 13/2014



የሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ የቦርድ እና የማኔጅመንት አባላት



የድርጅቱ ሰራተኞች በከፊል

## i. የቦርድ ሰብሳቢ መልዕክት



ክቡራት እና ክቡራን!

ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ላለፉት 28 ዓመታት በርካታ የማህበረሰብ ልማትን ያከናወነ እና ለሀገራዊ እና ዓለም አቀፍ የልማት ግቦች መሳካት የበኩሉን አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ የሚገኝ ሀገር በቀል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው፡፡

ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ፕሮግራሞቹን በማስፋት፤ የማህበረሰብ እና ክልላዊ ተደራሽነቱን በማሳደግ ከፍተኛ እመርታ እያሳየ ይገኛል፡፡ በበጀት ዓመቱ በአራት ክልሎች (ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ፤ ደቡብ ምእራብ፤ ሲዳማ ኦሮሚያ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ 120 ወረዳዎች/ቀበሌዎች የተቀናጀ የልማት ስራ በማከናወን በመቶ ሽህ የሚቆጠሩ ድጋፉ የሚያስፈልጋቸው የማህበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ተችሏል፡፡

ከማህበረሰቡ ችግር ስፋት እና ጥልቀት አንፃር በለጋሽ ድርጅት ድጋፍ ብቻ ብዙ ርቀት መሄድ እንደማይቻል የተረዳው ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ከ17 ዓመታት በፊት የኢትዮጵያዊያን ለኢትዮጵያዊያን ንቅናቄን (የመንግስት-ማህበረሰብ-የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አጋርነትን) እውን በማድረግና በማጠናከር ባለድርሻ አካላት በተለይም የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ በተደራጀ መንገድ ማህበራዊ ሃላፊነቱን እንዲወጣ ፋና ወጊ ስራ ሰርቷል፡፡ በበጀት ዓመቱም ምንም እንኳ በሀገር ደረጃ በነበረው አለመረጋጋት፤ የሰሜኑ ችግር፤የገበያ ግሽበት እና የኮሮና ተፅእኖ የፈጠረው ተፅእኖ ከፍተኛ ቢሆንም ይህን ተቋቁሞ በርካታ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ የበጀት አፈፃፀም ከእቅድ አንፃር 107% ማሳካት የተቻለ ሲሆን ይህም ከባለፈው ዓመት ሲነፃፀር በ19% እድገት አሳይቷል፡፡ የተሰባሰበው ሀብት ለዋና ዋና የልማት ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ እንዲውል ተደርጓል፡፡

በበጀት ዓመቱ የዝግጅት ምእራፍ የተከናወነባቸው የአንዳንዶቹም ስራው የተጀመረባቸው የአረጋዊያን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነትን የሚያሻሽሉ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት በሆሳዕና እና አርባምንጭ በቀጣይ ዓመት ግንባታቸውን የማፋጠን ስራ የሚተገበር ሲሆን በተመሳሳይ የድርጅቱን የልማት ስራዎች ዘለቄታዊነትን ለማረጋገጥ የሚያግዙ በአዲስ አበባ እና በሃዋሳ ሁለገብ አገልግሎት መስጫ ህንፃ እና የማሰልጠኛ ህንፃ ግንባታ በዝግጅት ምእራፍ ላይ ሲሆኑ አስፈላጊው የዲዛይን ማሻሻያ፤ ዝርዝር ስራዎች እና የግንባታ ፈቃድ የተዘጋጀላቸው በመሆኑ የግንባታ ሂደታቸው በልዩ ትኩረት የሚከናወን ይሆናል፡፡ በዚህ የበጀት ዓመት ድርጅቱ ካለው ወቅታዊ ሁኔታ ጋር ራሱን አጣጥሞ ለማስኬድ እና ውጤታማ ለመሆን ይችል ዘንድ በውጭ አማካሪዎች አስጠንቶ፤ በቦርድ አባላቱም የቅርብ ክትትልና ድጋፍ የመዋቅር ማሻሻያ ስራ ተከናውኗል፤ የሰው ኃብት አስተዳደር
መመሪያ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ያለፉትን ዓመታት ተሞክሮ እና አሁን ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስከበ ለ2014/15 የበጀት ዓመት የተሻለ እቅድ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

የበጀት ዓመቱን ስራዎቻችንን ለማሳካት በበጀት እና በዓይነት ድጋፍ ላደረጋችሁልን ደጋፊዎቻችንና አጋሮቻችን የመንግስት ተቋማት፤ ለጋሽ ድርጅቶች (የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ትብብር፤ ዓለም የስደተኞች ድርጅት፤ ዓለም አቀፍ የስነ-ህዝብ ፈንድ፤ ማቴዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ ፤ዓለም ባንክ/ ስራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ እንዲሁም የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች እና ዲያስፖራው ማህበረሰብ፤ በጎ አድራጊ ግለሰቦች በሙሉ ልባዊ ምስጋናዬን እያቀረብኩ ድጋፉ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሌሎችም እንድትሳተፉበት ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡ አመሰግናለሁ፡፡

ይስማሸዋ ስዩም
የቦርድ ሰብሳቢ

ሉናር ኢንተርናሽናል ኮሌጅ በአዲስ አበባ በየቀኑ 100 አረጋዊያንን ይመግባል፡፡





# የሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ የቦርድ አባላት



አቶ ይስማሸዋ ስዩም
የቦርድ ሰብሳቢ



አቶ አማረ ካሳ
የቦርድ ም/ሰብሳቢ



አቶ ካሳዬ ለማ
የቦርድ አባል



ወ/ሮ አዲስ ዘለቃው
የቦርድ አባል



ወ/ሮ ወርቅነሽ ዳባ
የቦርድ አባል



አቶ አይናለም ይግዛው
የቦርድ አባል



ወ/ሮ የምስራች ሀብታሙ
የቦርድ አባል

# ii. የዋና ስራ አስኪያጅ መልዕክት



እንደ ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ያቀድናቸውን የልማት ስራዎች ለማሳካት ከፍተኛ ጥረት አድርገናል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የፕሮግራሞቻችን የአገልግሎት ዘርፍ እየሰፋ እና ማህበረሰባዊ ተደራሽነታችንን እያሳደግን በመሄዳችን ከ205 ሽህ በላይ ለችግር የተጋለጡ ህፃናት፤ አሳዳጊዎች፤ ሴቶችን፤ ደጋፊ የሌላቸው አረጋዊያን፤ ወጣቶች በደማቸው ውስጥ የኤችአይቪ ቫይረስ ያለባቸው ወገኖችን በቀጥታ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በምንሰራባቸው ክልሎች እና የከተማ አስተዳደር በተዘዋዋሪ በልዩ ልዩ አገልግሎቶች ተደራሽ ሆነዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ 91 (ዘጠና አንድ) ሚሊዮን ብር ከለጋሽ ድርጅቶች እና ከሀገር ውስጥ ሀብት በማሰባሰብ የበጀት አፈፃፀማችንን ማሳደግ የቻልን ሲሆን በኢትዮጵያዊያን ብቻ የስፖንሰርሺፕ ድጋፍ የሚያገኙ ህፃናትን እና አረጋዊያንን ቁጥር በ14% ማሳደግ ችለናል፡፡ ከሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የፌደራል ሚኒስቴር መ/ቤቶችን ከፍተኛ የማነቃነቅና የማስተባበር ስራ በመስራት በበጀት ዓመቱ 60 ህፃናት በሚኒስቴር መ/ቤቶች በስፖንሰርሺፕ ድጋፍ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ከዓለም ባንክ በተገኘ በጀት የከተማ ልማት ፕሮጀክትን ከሃዋሳ አረጋዊያን ማዕከል ጋር በማጣመር ለችግር የተጋለጡ አረጋዊያን የተቀናጀ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል፡፡

ከተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶች በተገኘ የበጀት ድጋፍ እና ከሀገር ወስጥ በተሰባሰበ ሀብት በመታገዝ የታቀዱ ፕሮጀክቶቻችንን በጥሩ ሁኔታ መፈፀም ችለናል፡፡

የድርጅቱን ፕሮግራሞች የመፈፀም አቅሙን ለማሳደግ የሰው ሀብቱን በስልጠና እና አቅም ግንባታ ድጋፎች ለማጠናከር ጥረት ተደርጓል፡፡ ከዚህ በላይ ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ የመንግስት-የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አጋርነት (ኢትዮጵያዊያን ለኢትዮጵያዊያን) ፕሮግራም መልካም ተሞክሮዎቹን ለሌሎች ከተሞች በማካፈል እና በአጋርነት በመስራት የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት ፕሮራሞቻችንን ወደ ሌሎች ክልሎች ለማስፋት የግንኙነት እና አጋርነት ስራዎች ተጀምረዋል፤ ይህም በሚቀጥለው የበጀት ዓመት ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

ያቀድነውን በመልካም ሁኔታ እንድንፈፅም የድርጅቱ ሰራተኞች እና በጎ ፈቃደኞች ላደረጉት ጥረት እና ትጋት እንዲሁም ለጋሽ ድርጅቶች፡ የመንግስት-የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ፤ ስፖንሰሮች፡ የዲያስፖራው ማህበረሰብና በጎ አድራጊ ግለሰቦች በገንዘብና በልዩ ልዩ ድጋፍ ላደረጉልን ሁሉ ምስጋናዬን እያቀረብኩ የድርጅቱ የጠቅላላ ጉባኤ እና የቦርድ አባላት ለነበራቸው የላቀ የአመራርነት ሚና ከፍተኛ አክብሮቴን መግለፅ እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም ለቀጣይ ዓመት ከዚህ የተሻለ ውጤት ለማምጣት በትጋት እንደምንሰራ በዚህ አጋጣሚ መግለፅ እፈልጋለሁ፡፡ ***“ሁሌም ስሰጥ የምቀበለው አለኝ”*** የሚለው መሪ ሃሳብ በጥሩ ውጤቶች እና ስኬቶች ታጅቦ ወደ ፊት ይቀጥላል፡፡

ሲ/ር ዘቢደር ዘውዴ
መስራችና ዋና ስራ አስኪያጅ

# የማኔጅመንት አባላት



ሲ/ር ዘቢደር ዘውዴ
መስራች እና ዋና ስራ አስኪያጅ



አቶ ስንታየሁ ኃይሉ
ፕሮግራም ዳይሬክተር



አቶ ቴዎድሮስ ካሳሁን
ቺፍ ኦፍ ፓርቲ



አቶ ታደሰ ተስፋዬ
ፋይናንስ ኃላፊ



አቶ ጌትነት ተስፋ
የሰው ሀብት አስተዳደር ኃላፊ



አቶ ወንድወሰን መሰለ
ክትትል እና ግምገማ ማናጀር

# 1. መግቢያ

ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ከተመሰረተ 28 ዓመታትን አስቆጥሯል። በእነዚህ ዓመታት 4 የአምስት ዓመታት ስትራቴጂክ እቅዶችን እውን በማድረግ በርካታ ውጤቶችን እና የልማት አሻራዎችን ማስቀመጥ የቻለ ድርጅት ነው። በ2013/14 በጀት ዓመት ህፃናትን፤ ሴቶችን፤ ለኤችአይቪ/ኤድስ ተጋላጭ የሆኑ ወገኖችን፤ ወጣቶችን፤ አረጋዊያንን እንዲሁም ሌሎች ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተደራሽ ያደረጉ የተቀናጁ የልማት ስራዎችን በኢኮኖሚ አቅም ግንባታ፣ ትምህርት፣ ጤና፤ ስርዓተ-ፆታን፣ የተቀናጀ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልን፣ ድጋፍ እና ክብካቤን፣ የአፍላ ወጣቶች ስነ ተዋልዶ ጤና የመሳሰሉትን ስራዎች አከናውኗል። ስራዎቹ የተከናወኑት በአዲስ አበባ በአምስት ክፍለ ከተሞች ማለትም በየካ፣ጉለሌ፣አዲስ ከተማ፣ ቦሌ እና ኮልፌ ቀራኒዮ እንዲሁም በደቡብ ክልል በሃዲያ፣ ወላይታ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ጉራጌ፣ ጋሞ ዞኖች፤ በሲዳማ ክልል በሃዋሳ እና ይርጋለም ከተሞች፤ በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልል በቤንች ማጂ እና ሸካ ዞኖች፤ በተጨማሪም በኦሮሚያ ክልል ቢሾፍቱ ከተማ በአጠቃላይ በ120 ወረዳዎች እና ቀበሌዎች ነው።

በሪፖርት ዘመኑ በትምህርት ልማት ዘርፍ 61,841 ህፃናት ተጠቃሚ ሆነዋል፤በጤናው ዘርፍ 112,803 የህብረተሰብ ክፍሎች በመከላከል ላይ የተመሰረተ የጤና አገልግሎት አግኝተዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ 23,310 ዜጎች ድርጅቱ ባሉት ሁለት የህክምና ማእከላት እና ከመንግስት የጤና ተቋማት በቅብብሎሽ የህክምና አገልግሎት አግኝተዋል። በኢኮኖሚ አቅም ግንባታ ዘርፍ 8,017 ሴቶችና ወጣቶች ራሳቸውን የሚያስችል ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን እገዛ 3,313 ለችግር የተጋለጡ ህፃናትና አረጋዊያን ወርሃዊ የስፖንሰርሺፕ ድጋፍ ተጠቃሚ ሆነዋል። በሆሳዕና እና አርባ ምንጭ ከተሞች የሁለት አረጋዊያን ማዕከላት ግንባታ ስራዎች ተጀምረዋል። እንዲሁም በአዲስ አበባ ሁለገብ አገልግሎት መስጫ ህንፃ ለመገንባት የዝግጅት ስራዎች በመከናወን ላይ ናቸው።

የፋይናንስ አፈፃፀማችንን በምንመለከትበት ጊዜ 91,348,436.13 ብር ገቢ ከለጋሽ ድርጅቶች፤ ከሀገር ውስጥ ባለሃብቶች እና ከዲያስፖራው ማህበረሰብ ማግኘት ተችሏል። ከወጭ አንፃር 87,861,993.88 ብር ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ይህም በአጠቃላይ ለበጀት ዓመት ከነበረው በጀት 79% የሚሸፍን ነው። የተከናውኑት ስራዎች ክፍል 2 በዝር ዝር የቀረቡ ሲሆን የሚከተሉት ጥቂት ገፆች የበጀት ዓመቱን የዋና ዋና አገልግሎቶች ጥቅል አፈፃፀም የሚያመለክቱ ናቸው።

## 2. የተግባራት እና በጀት ዓመታዊ አፈፃፀም

### የተጠቃሚዎች ተደራሽነት በአገልግሎት ዘርፍ

በ2013/2014 የበጀት ዓመት 1.6 ሚሊዮን የህብረተሰብ ክፍል በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተደራሽ ሆኗል። ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች 205,971 ናቸው።

**ትምህርት አገልግሎት**

61,841 (164%)

- የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ
- የማጠናከሪያ ትምህርት አገልግሎት
- የትምህርት አፈፃፀም ክትትልና ምክር አገልግሎት
- ነፃ ትምህርት ድጋፍ
- የቤተ-መፃህፍት እና ኮምፒዩተር ስልጠና አገልግሎት

**ጤና አገልግሎት**

136.113 (92%)

የጤና መከላከል እና ህክምና

- ኤችአይቪ/ኤድስ መከላከል፣ ምርመራ፣ ድጋፍና ህክምና
- የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር መከላከልና ህክምና
- የሳንባ ካንሰር መከላከልና ህክምና
- ቤተሰብ ምጣኔ
- ስነ-ተዋልዶ ጤና
- እናቶችና ህፃናት ጤና
- ህክምና አገልግሎት

**የመንግስት- የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አጋርነት**

3,312 (101%)

- የህፃናት እና አረጋዊያን ስፖንሰርሺፕ
- የምግብ፣ አልባሳት፣ የንፅህና መጠበቂያ እና ልዩ ልዩ ቁሳቁስ ድጋፍ
- የስራ እድል ማመቻቸት

**የኢኮኖሚ አቅም ግንባታ**

8,017 (160%)

- የራስ አገዝ የቁጠባ ቡድኖችን ማጠናከር
- የገቢ ማስገኛ ስራዎች
- የንግድ ክህሎትና ሂሳብ አያያዝ ስልጠና
- የሙያ ክህሎት ስልጠና
- መነሻ ካፒታል እና የዓይነት ድጋፍ
- የገበያ ትስስር

- በሀገር ውስጥ ሀብት ብቻ ወርሃዊ የስፖንሰርሽፕ ድጋፍ የሚያገኙ ህፃናት እና አረጋዊያን 3,313 ደርሷል፡፡ ከ2012/13 የ14% ጭማሪ አለው፡፡



## 2.1 የኢኮኖሚ አቅም ግንባታ

ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ አቅም ግንባታ ዘርፍ የተጠቃሚዎችን በተለይም የህፃናት አሳዳጊዎችን፤ ለችግር የተጋለጡ ሴቶች እና ስራ አጥ ወጣቶችን ህይወት የሚቀይሩ እና በዘላቂነት ራሳቸውን እንዲችሉ የሚያግዙ የተለያዩ ስራዎችን ለዓመታት ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በበጀት ዓመቱ የ5,000 በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል እቅድ ተይዞ የነበረ ሲሆን መልካም አፈፃፀም ታይቶበታል፡፡

- 6,310 (>100%) አባላት ያሳቸው የ393 የራስ አገዝ ቁጠባ ቡድኖች፤41 ከስደት ተመላሽ ወጣቶች የስራ ፈጠራ እና ሙያ ክህሎት፤ በንግድ እና በገበያ ትስስር ስልጠና ያገኙ ሲሆን መስራት የሚችሉ ነገር ግን ችግረኛ የሆኑ 454 የህፃናት አሳዳጊዎች እና ከስደት ተመላሽ ወጣቶች መነሻ የዓይነት ድጋፍ በጥቅሉ 3,002,000.00 ብር የሚገመት ለአሳዳጊዎች ብር 3,000 ለወጣቶቹ ደግሞ እስከ ብር 40,000 ለእያንዳንዳቸው ተሰጥቷቸው በአትክልትና ፍራፍሬ፤ እንጀራ፤ የባልትና ውጤቶች፤ ከሰል፤ በከብት ማደለብ፤ በእህል ንግድ፤ በአልባሳትና በችርቻሮ ሱቅ የገቢ ማስገኛ ስራቸውን በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡ በባለሙያ የቅርብ ክትትል እና ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ በተሰማሩበት የገቢ ማስገኛ ስራ ውጤታማ መሆን ችለዋል፡፡
- በራስ አገዝ የቁጠባ ቡድን የተደራጁ ተጠቃሚዎች የአስተሳሰብ እና የአመለካከት ለውጥ በማምጣት ቁጠባቸውን በመሳደግ ረገድ ከፍተኛ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ የራስ አገዝ ቁጠባ ቡድኖች አባላት 4,037,332.42 ብር የቆጠቡ ሲሆን አባላት በሚያቀርቡት የገቢ ማስገኛ ስራ እቅድ መሰረት ብር 1,100,101.00 የብድር አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ ከወሰዱት ብድር ውስጥ ብር 977,134.00 (89%) ተመላሽ አድርገዋል፡፡ ይህም አባላት ቁጠባቸውን የማሳደግ እና ብድር የመመለስ ብቃታቸውን እንደጨመሩ ያሳያል፡፡







*ሴቶች እና ወጣቶች የተሰማሩባቸው የገቢ ማስገኛ ተግባራት በከፊል*

- ለ75 ያታዊ ጥቃት ተጋላጭ ለሆኑ ሴት የወሲብ ንግድ ላይ የተሰማሩ፤ ሌሎች ተጋላጭ ልጃገረዶችና ሴቶችን በማህበረሰብ ራስ አገዝ ቡድን በማዋቀርና የቴክኒክ ስልጠና ለመስጠት ከታቀደው ውስጥ 55 (73%) ተደራሽ ሆነዋል፡፡
- በወጣቶች ላይ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት ሰርቶ መለወጥ በሀገር የሚል ዓላማ ያደረገ በሃዲያ ዞን ሆሳዕና ከተማ የዞኑ ሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ፤ ሴቶች እና ህፃናት ጉዳይ መምሪያዎች፤ የከተማ አስተዳደር፤ የት/ቤት ማህበረሰብ እና የሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ተወካዮችም በተገኙበት የስደትን አስከፊነት የሚያስተምሩ የንቅናቄ ስራዎች፤ የውይይት ፕሮግራሞች፤ የስፖርት ውድድሮች፡ ተከናውነዋል፡፡ በግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃግብሩ 50,000 የሚገመት የማህበረሰብ ክፍል ተደራሽ ሆኗል፡፡





*የወጣቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሁነቶች በሃዲያ ዞን፤ ሆሳዕና ከተማ*

# 2.2 ትምህርት

## 2.2.1 የትምህርት ተደራሽነት

- ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ፕሮጀክቶቹን በሚተገብርባቸው አካባቢዎች በ2013/14 የበጀት ዓመት በፕሮጀክቶች የታቀፉ 37,338 ህፃናትና እና 8,297 አሳዳጊዎች በቤት ለቤት ክትትል የትምህርት የምክር አገልግሎት ድጋፍ ተደራሽ ሆነዋል፡፡
- የፕሮጀክት በጀትን በመጠቀም፤ የመንግስት-ማህበረሰብ - የግል ባለሃብቱን አጋርነት በማጠናከር ከማህበረሰብ በተሰባሰበ የዓይነት ድጋፍ 8,024 ህፃናት በትምህርት መርጃ ቁሳቁሶች (ደብተር፤ እስክሪብቶ፤ እርሳስ እና የመሳሰሉት) ድጋፍ ተጠቃሚ በማድረግ በትምህርት መርጃ ቁሳቁሶች ችግር ትምህርታቸውን ለማቋረጥ የሚገደዱ በርካታ ህፃናትን መታደግ ተችሏል፡፡
- በአንዳንድ ት/ቤቶች ለልማት አስተዋፅኦ የሚጠየቁ ክፍያዎችን መክፈል ሳልቻሉ 31 ህፃናት ከት/ቤቶቹ ጋር በመነጋገር ከክፍያ ነፃ እንዲሆኑ እና ትምህርታቸውን ተረጋግተው እንዲማሩ ተደርጓል፡፡

## 2.2.2 የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የተሰሩ ስራዎች

- 24,503 ህፃናት እና ወጣቶች በሀዋሳ ህፃናት እና ወጣቶች ማዕከል የቤተ መፃህፍት አገልግሎት እና 45 ህፃናትና ወጣቶች የኮምፒዩተር ስልጠና ተጠቃሚ በመሆናቸው የንባብ ባህላቸው እንዲጎለብት፤ እውቀታቸውና አመለካከታቸው እንዲሰፋ፤ መሰረታዊ የኮምፒተር ክህሎት እንዲኖራቸው እና በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል ድጋፍ አግኝተዋል፡፡

- በሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ድጋፍ በወጣቶች ማዕከል ኮምፒዩተሮች ጥገና ተደርጎላቸው ለተጠቃሚዎች የስልጠና እድሎችን መፍጠር ተችሏል፡፡
- 100,000 ብር የሚያወጣ የመፃህፍት ድጋፍ በሃዲያ ዞን ለሚገኙ 2 ት/ቤቶች ድጋፍ በማድረግ የትምህርት ጥራትን በማሻሻል በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡




*ከዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት ጋር በመተባበር በሃዲያ ዞን ለት/ቤቶች የመፃህፍት ድጋፍ ሲደረግ*

# 2.3 ጤና

ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ፕሮጀክቶች በሚተገብርባቸው አካባቢዎች በጤና መከላከል፤ ድጋፍ እና ህክምና አገልግሎት ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል፡፡

### 2.3.1 ስነ- ተዋልዶ ጤና፤ ፆታ ተኮር፤ ኮሮና እና ሌሎችም

- 48,337 ህፃናት እና ወላጆች/ አሳዳጊዎች በማህበረሰብ ጤና ሰራተኛ አማካኝነት ስለ ንፅህና አጠባበቅ እና ኮሮና በሽታ መከላከል ትምህርት አግኝተዋል
- 12,981 ወጣቶች፤ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማህበረሰብ ፤ የአዲስ አበባ እና የሃዋሳ የኢንዱስትሪ ፓርክ ሰራተኞች፤ እንዲሁም በማህበረሰብ ሬዲዮ 45,000 የማህበረሰብ ክፍሎች በስነ ተዋልዶ ጤና እና ፆታ ተኮር ጥቃትን በመከላከል ላይ ያተኮረ ትምህርት ተደራሽ ሆነዋል፡፡ 3,850 የግንዛቤ ማስጨበጫ ፅሁፎችም ተሰራጭተዋል

### 2.3.2 የሳንባ ካንሰር መከላከል እና ህክምና

- ለ37,513 የህብረተሰብ ክፍሎች ስለ ሳንባ ካንሰር ትምህርት ተሰጥቷቸዋል፡፡
- 28,169 የማህበረሰብ ክፍል በማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን በሳንባ ካንሰር ትምህርት ተደራሽ ሆኗል፡፡
- 268 የኢንዱስትሪ ሰራተኞች የሳንባ መከላከል ትምህርት ተሰጥቷቸዋል፡፡

### 2.3.3 የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር መከላከል እና ህክምና

ለ5,177 ሰዎች ስለ ማህፀን ጫፍ ካንሰር ትምህርት ተሰጥቷቸዋል

597 ሴቶች በቅድመ ካንሰር ምርመራ ተደራሽ ሆነዋል፡፡


በምርመራ ውጤታቸው የቫይረስ ምልክት የታየባቸው 33 ሴቶች የተሻለ ምርመራ እና ህክምና አገልግሎት አግኝተዋል፡፡

### 2.3.4 ህክምና አገልግሎት

- በአዲስ አበባ እና በሃዋሳ በሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ክሊኒኮች 22,521 የማህበረሰብ ክፍል የህክምና አገልግሎት ማግኘት ችለዋል
- 2,644 ህፃናት የክትባት አገልግሎት አግኝተዋል፡፡
- 443 ተጠቃሚዎች ኤችአይቪን ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍን በመከላከል አገልግሎት ተደራሽ ሆነዋል፡፡
- 1,224 ተጠቃሚዎች ደግሞ በቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተደራሽ ሆነዋል፡፡

### 2.3.5 ኤችአይቪ/ኤድስ

- 3,400 ኤችአይቪ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ሰዎች ጤንነታቸውን በተሻለ ይንከባከቡ ዘንድ በፕሮጀክቱ የተለያዩ ማህበራዊ-ስነልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
- 20,533 ልዩ ልዩ የኤችአይቪ መመርመሪያ ግብአቶች ስርጭት ተከናውኗል፡፡
- ለ4,847 ሰዎች የኤችአይቪ ምርመራ አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን አዲስ በደማቸው ውስጥ ኤችአይቪ ቫይረስ የተገኘባቸው 278 ሰዎች የፀረ-ኤችአይቪ እና ሌሎች የህክምና አገልግሎቶችን ማግኘት ችለዋል፡፡
- የራስ በራስ የኤችአይቪ ኤድስ ምርመራ ለ2,444 ሰዎች ተደራሽ ሆኗል
- 291 የፀረ-ኤችአይቪ መድሃኒት ክትትል ያቋረጡ ሰዎች እንደገና መድሃኒቱን እንዲጀምሩ ተደርጓል
- 1,162 ኤችአይቪ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ሰዎች የማህበረሰብ አቀፍ የፀረ-ኤችአይቪ መድሃኒት በአካባቢያቸው በቅርብ የሚያገኙበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡






*ስነ ተዋልዶ ጤና ግንዛቤ ማስጨበጫ በሃዋሳ ወጣት ማዕከል*



*የሳንባ ካንሰር ስልጠና ለጤና ባለሙያዎች*

**ግራፍ 1፡ የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር መከላከልና ህክምና አገልግሎት**




- ለ1,405 የህብረተሰብ ክፍሎች የቅድመ ምርመራ ልየታ ስራ በማከናወን 53 ሰዎች ለሳንባ ካንሰር ምርምራ አገልግሎት ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ሪፈራል ሆስፒታል ተልከዋል፡፡







*የሳንባ ካንሰር ትምህርት በጤና ተቋማት*

- የኤች አይቪ ስርጭትን ለመግታት ያስችል ዘንድ በበጀት ዓመቱ ከኤችአይቪ ጋር የሚኖሩ ነገር ግን የፆታዊ ግንኙነት ያላቸውን እና የትዳር አጋሮቻቸውን እና የወለዷቸውን ልጆች ያላስመረመሩትን ሰዎች ከጤና ተቋምና ከማህበረሰቡ በተሰባሰበ መረጃ ለ4,847 ሰዎች የምርመራ አገልግሎት በመስጠት ከተመረመሩት 278 ሰዎች (6%) በደማቸው ውስጥ ኤችአይቪ ቫይረስ የተገኘባቸው ሲሆን የፀረ-ኤችአይቪ እና ሌሎች የህክምና አገልግሎቶችን ወዲያዉኑ እንዲያገኙ ተደርጓል። ከዚህ በታች የተመለከተው ግራፍ 2 ኤችአይቪ በደማቸው ውስጥ የተገኘባቸው ከእነሱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሰዎች ለማስመርመር የተሰጣቸውን የምክር አገልግሎት ጨምሮ በምርመራ ሂደቱ ያለፉ ሰዎችን ዝር ዝር ያሳያል።

**ግራፍ 2፡ ማህበረሰብ አቀፍ የኤችአይቪ ምርመራ አፈፃፀም**



## 2.4 የመንግስት - ማህበረሰብ - የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አጋርነት

ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ፕሮጀክቶቹን በሚያከነውንባቸው አካባቢዎች በ2013/14 ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያዊያን ፕሮጀክት የማህበራዊ ዋስትና ደህንነት ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል፡፡

### 2.4.1 ስፖንሰርሺፕ

- በበጀት ዓመቱ 2,802 ህፃናት በየወሩ ብር 450 ለእያንዳንዳቸው ከሃገር ውስጥ ደጋፊዎች በቋሚነት የስፖንሰርሺፕ ድጋፍ አግኝተዋል፡፡
- አረጋዊያንን በስፖንሰርሺፕ ተጠቃሚ ከማድረግ አንፃር በሪፖርት ዘመኑ 511 አረጋዊያን በየወሩ ብር 450 ለእያንዳንዳቸው ከሃገር ውስጥ ደጋፊዎች በቋሚነት የስፖንሰርሺፕ ድጋፍ ማግኘት ችለዋል፡፡




*ዶ/ር እመቤት 25 ህፃናትን ስፖንሰር አድርገዋል*

- ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ከሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ባከናወኑት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ የፌደራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች 60 ልጆችን ስፖንሰር ያደረጉ ሲሆን ከሚደግፏቸው ህፃናት ጋር በብሄራዊ ቤተመንግስት አንድነት ፓርክ ክብርት ቀዳማዊት ዝናሽ ታያቸው እና ሚኒስትሮች፤ የሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ቦርድ አመራሮች በተገኙበት ደማቅ የትውውቅ ስነ ስርዓት ተከናውኗል፡፡ በወቅቱ 320 ልጆችን ስፖንሰር ለማድረግ ቃል የተገባ ሲሆን በሂደት ሁሉም ሚኒስቴር መ/ቤቶች ወደ ድጋፉ እንደሚገቡ ይጠበቃል፡፡



በመርሀግብሩ ላይ የተገኙ ቀዳማዊት እመቤት፣ የጠቅላይ ፍርድቤት ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ አቃቤ ህግ እና ሚኒስሮች

## 2.4.2 ሀብት ማሰባሰብ / ልገሳ

- ግምታቸው 7,951,020.63 ብር የሚሆን የዓይነት ድጋፎችን የቀን አልባሳት፣ ብርድ ልብስ፣ የምግብ ዓይነቶች፣ የንፅህና መጠበቂያ፣ የምግብ ማብሰያ እና መመገቢያ ቁሳቁስ፣ የቢሮ እቃዎች፣ የትምህርት መርጃ ቁሳቁስ የመሳሰሉት ከማህበረሰቡና ከባለሀብቱ በልገሳ የተገኙ ሲሆን ለ3,416 ህፃናትና አረጋዊያን ተሰራጭቷል፡፡







*በአዲስ አበባ እና በሃዋሳ ለ859 ተጠቃሚዎች (508 ህፃናት እና 351 አረጋዊያን) ከማህበረሰቡ በተሰባሰበ የምግብ ድጋፍ ተደራሽ ሆነዋል፡፡*



በመርሀግብሩ ላይ የተገኙ ቀዳማዊት እመቤት፣ የጠቅላይ ፍርድቤት ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ አቃቤ ህግ እና ሚኒስሮች

## 2.4.2 ሀብት ማሰባሰብ / ልገሳ

- ግምታቸው 7,951,020.63 ብር የሚሆን የዓይነት ድጋፎችን የቀን አልባሳት፣ ብርድ ልብስ፣ የምግብ ዓይነቶች፣ የንፅህና መጠበቂያ፣ የምግብ ማብሰያ እና መመገቢያ ቁሳቁስ፣ የቢሮ እቃዎች፣ የትምህርት መርጃ ቁሳቁስ የመሳሰሉት ከማህበረሰቡና ከባለሀብቱ በልገሳ የተገኙ ሲሆን ለ3,416 ህፃናትና አረጋዊያን ተሰራጭቷል፡፡




*በአዲስ አበባ እና በሃዋሳ ለ859 ተጠቃሚዎች (508 ህፃናት እና 351 አረጋዊያን) ከማህበረሰቡ በተሰባሰበ የምግብ ድጋፍ ተደራሽ ሆነዋል፡፡*



*አረጋዊያን የምግብ አገልግሎት ሲሰጣቸው በሜሪ ጆይ አስኮ ግቢ*

- የድርጅቱ ሰራተኞች ከወር ደመወዛቸው በመቁረጥ በጦርነቱ ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው እና ለተፈናቀሉ ሰዎች በሸዋሮቢት የምግብ ቁሳቁስ፣ ዱቄት፣ ማካሮኒ፣ አልባሳት እና የሴቶች ንፅህና መጠበቂያ ድጋፍ አድርገዋል፡፡

በአጠቃላይ የተደረገው ዓይነት ልገሳ ድጋፍ ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ላይ ተጠቅሷል

| ተ.ቁ. | የድጋፍ ዓይነት | በአዲስ አበባ | በክልል ከተሞች | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የምግብ ቁሳቁስ ድጋፍ | 57,762.72 | 1,509,106.00 | 1,566,868.72 |
| 2 | የትምህርት ቁሳቁስ | 1,221,630.00 | | 1,221,630.00 |
| 3 | የንፅህና መጠበቂያ | 62,050.00 | 200,000.00 | 262,050.00 |
| 4 | አልባሳት | 2,111,200.00 | 155,000.00 | 2,266,200.00 |
| 5 | ያገለገሉ የቢሮ እቃዎች | 1,804,321.91 | 192,000.00 | 1,996,321.91 |
| 6 | የህክምና ድጋፍ | | 104,150.00 | 104,150.00 |
| 7 | የልዩ ልዩ ሙያ ድጋፍ | | 292,800.00 | 292,800.00 |
| 8 | ቲቪኤስ ባጃጅ ልገሳ | | 241,000.00 | 241,000.00 |
| | ድምር | **5,256,964.63** | **2,694,056.00** | **7,951,020.63** |

## 2.4.3 ሃዋሳ አረጋዊያን ማዕከል

- በሃዋሳ አረጋዊያን ማዕከል በየቀኑ ከ100 ያላነሱ አረጋዊያን የምግብ፣ የማህበራዊ፣ ስነልቦናዊ፣ የጤና እና የመዝናኛ አገልግሎቶችን በማግኘት ላይ ናቸው፡፡
- ከአረጋዊያን ማዕከሉ ውጭ ላሉ፣ ቤት ለዋሉ 20 አቅመ ደካማ አረጋዊያን በየቀኑ የምግብ አገልግሎት እንዲቀርብላቸው ተደርጓል፡፡

- 120 ለጎዳና ህይወት እና ለችግር የተጋለጡ አረጋዊያን ወደ የከተማ ልማት ድጋፍ ፕሮጀክት እንዲገቡና በአረጋዊያን ማዕከሉ የአዳሪ የተቀናጀ አገልግሎት እንዲታቀፉ ተደርጎ አስፈላጊው እንክብካቤ እና ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡

- በተጨማሪም 29 ለጎዳና ህይወት ተጋላጭ የነበሩ እና ከፍተኛ ችግር የነበረባቸውን አረጋዊያን ተከታታይ የምክር አገልግሎት በመስጠት፤ ቤተሰቦቻቸውን በማፈላለግ እና ምክክር በማድረግ ወደ ቤተሰቦቻቸው እንዲቀላቀሉ ተደርጓል፡፡

- በሃዋሳ አረጋዊያን ማዕከል አረጋዊያኑን ያሳተፈ እና ያነቃቃ የጓሮ አትክልት ልማት የተከናወነ ሲሆን ግምቱ ብር 3,000 የሚሆን የበቆሎ፤ ቦሎቄ፤ ቆስጣ፤ ሰላጣ እና ካሮት ተመርቶ ለአረጋዊያኑ አገልግሎት እንዲውል ተደርጓል፡፡
- የማዕከሉን የእለት ተእለት ስራ ለማከናወን እና የቤት ለቤት የአረጋዊያን የምግብ አገልግሎቱን በአግባቡ ለመስራት የመኪና ችግር ስለነበር ይህን የተረዳው የደቡብ ክልል ብልፅግና ቢሮ የ241,000 ብር ባጃጅ ልገሳ አድርጓል፡፡



*በሃዋሳ አረጋዊያን ማዕከል የምግብ አገልግሎት ሲሰጥ*

## 2.4.4 የአረጋዊያን ማዕከላት ፕሮጀክቶች

### → የሆሳዕና አረጋዊያን ማዕከል ግንባታ

ክብርት ዶ/ር ኤርጎጌ ተስፋዬ የኢፌድሪ ሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር በተገኙበት ከሆሳዕና ከተማ አስተዳደር በተለገሰልን 5,000 ካሬ ሜትር መሬት ላይ የመሰረት ድንጋይ ከተቀመጠ በኋላ የተለያዩ ኩነቶችን በማካሄድ በዓይነት ቃል የተገባ ግምቱ 10 ሚሊዮን ብር የሚሆን ድጋፍን ሳይጨምር ከማህበረሰቡ እና ከመንግስት 1,639,279 ብር በማሰባሰብ የግንባታ ስራው እንዲጀመር ተደርጓል፡፡ እስካሁን ድረስ 352,425.10 ብር ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ ለማዕከሉ ግንባታ ማስፈፀሚያ በእቅድ የተያዘው 50 ሚሊዮን ብር ሲሆን ጭረት የወጣት አርክቴክቶች ማህበር በበጎ ፈቃደኝነት የማዕከሉን ዲዛይን እና ዝር ዝር ስራዎች በነፃ በማዘጋጀት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡




*የሆሳዕና አረጋዊያን ማዕከል ግንባታ የመሰረት ድንጋይ ሲቀመጥ*

## → የአርባ ምንጭ አረጋዊያን ማዕከል ግንባታ

በተመሳሳይ የአርባ ምንጭ አረጋዊያን ማዕከል ግንባታ የከተማ አስተዳደሩ በሰጠው ቦታ ላይ ለማከናወን የሀብት ማሰባሰብ ስራዎች በመካሄድ ላይ ናቸው። ለማዕከሉ ግንባታ ማስፈፀሚያ በእቅድ የተያዘው ብር 70 ሚሊዮን ብር ሲሆን በበጀት ዓመቱም የሩጫ ውድድርን ጨምሮ ሁሉ አቀፍ የሆነ፤ የመንግስት፤ የግል ተቋማት እና ማህበረሰቡን ያሳተፉ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች ተከናውነዋል። በዚህም መሰረት በዓይነትና በገንዘብ 4,695,907.81 ብር ሀብት ማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን ለግንባታው የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት ማስፈፀሚያ 65,029.50 ብር ወጪ ተደርጓል።



*ለአረጋዊያን ማዕከላት ግንባታ የማህበረሰብ ንቅናቄ እና ሃብት አሰባሰብ በአርባ ምንጭ*

## → የአዲስ አበባ ሁለገብ ህንፃ ግንባታ

ከኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ የግንባታ ፈቃድ ጽ/ቤት በተሰጠው አስተያየት መሰረት የህንፃው ዲዛይን የአደጋ ጊዜን ጨምሮ 2 የመውጫ በር፤ ሊፍት፤ ቤዝመንትና ፓርኪንግ የእንዲኖረው ተደርጎ ተሻሽሏል።

የማዕከሉ ግንባታ ዲዛይን ብሉ ፕሪንት እና ዝር ዝር ተግባራት ተዘጋጅተዋል። የሃብት ማሰባሰብ ስራዎች ቀጥለዋል። ሌሎችም የግንባታ ዝግጅት ምእራፎች ተከናውነዋል።

## 2.4.5 አባልነት

- የሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ አባላት ቁጥር የጨመረ ሲሆን በአዲስ አበባ እና በሃዋሳ 297 የግለሰብ አባላት እና 13 የድርጅት አባላት ይገኛሉ።

## 2.4.6 የበጎ ፈቃድ አገልግሎት

- የተለያየ ማህበራዊ መሰረት እና ሙያ ያላቸው የኪነጥበብ ባለሙያዎች፤ ደራሲያን፤ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች፤ የዩኒቨርሲቲ/ኮሌጅ ተማሪዎች፤ ከማህበረሰቡ የተውጣጡ በርካታ ሰዎች በድርጅቱ ፕሮጀክቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ይሰጣሉ። ከዚህም ውስጥ 1,200 የሚሆኑት በለጋሽ ድርጅቶች ድጋፍ በምናከናውናቸው ፕሮጀክቶች ውስጥ የሚሳተፉ ሲሆን ከ1,000 ያላነሱ በመንግስት-የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አጋርነት ፕሮግራሞች በሚሰራባቸው አዲስ አበባ፤ ሃዋሳ፤ ሆሳዕና እና አርባምንጭ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ይሰጣሉ።
- በጎ ፈቃደኞች በሀብት አሰባሰብ፤ በማህበረሰብ ንቅናቄ፡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በማከናወን፤ በቤት ለቤት ድጋፍ በመስጠት፤ ተጠቃሚዎችን በመንከባከብ፤ ለህፃናት የማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት በመሳሰሉት ተግባራት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል።




በጎ ፈቃደኞች በአዲስ አበባ

- በበጀት ዓመቱ ለረጂም ዓመታት በእውቀታቸው፤ በጉልበታቸው፤ በማህበራዊ ቅቡልነታቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረጉ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች፤ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች፤ ደራሲያን፤ ሰዓሊያን እና ሌሎችም የሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ቦርድ እና የማኔጅመንት አባላት በተገኙበት በአዳማ ከተማ የእውቅና እና ምስጋና ፕሮግራም ተዘጋጅቶላቸዋል። በወቅቱም ለበርካታ ዓመታት የበጎ ፈቃደኞች ኮሚቴን ሲመሩ እና ሲያስተባብሩ የነበሩ አንጋፋ አርቲስቶችን በሌሎች የመተካት ስነ ለነባሮቹ የበጎ ፍቃደኞች ኮሚቴ አመራሮች ለእነ አርቲስትአብራር አብዶ እና አጋሮቹ የድርጅቱ ቦርድ እና ስራአመራር አክብሮትንና ምስጋናውን አቅርቧል።

ስርዓት ተካሂዶ በቀጣዮቹ ጊዚያት እንዲመሩ አርቲስት ታምሩ ብርሃኑ፤ አርቲስት ትእግስት ግርማ ተመርጠዋል፡፡




የሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ በጎ ፈቃደኞች እውቅና ፕሮግራም በአዳማ




ጋዜጠኛ ሰለሞን ኃይለየሱስ የሜሪ ጆይ የበጎ ፈቃድ አምባሳደር ሆኖ ተመርጧል

## 3. አስተዳደር እና አመራር

የጠቅላላ ጉባኤው፤ ቦርዱ እና የስራ አመራር ኮሚቴው ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ የተሻለ የመፈፀም እና ማስፈፀም አቅም እንዲኖረው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

ከመንግስት እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፤ ከግሉ ሴክተር፤ ከማህበረሰብ ምስርት እና ከእምነት ተቋማት፤ ከመገናኛ ብዙሃንና ከኪነጥበብ ዘርፍ፤ ከትምህርት ተቋማት የተውጣጡ 60 አባላት ያሉት የጠቅላላ ጉባኤ በዓመት እየተሰበሰበ የዓመታዊ የስራ እና በጀት አፈፃፀም፤ የኦዲት ሪፖርት እና የቀጣይ ዓመት እቅድን ፤ ፖሊሲዎችንና ደንቦችን መርምሮ ያፀድቃል። አቅጣጫም ያስቀምጣል።

ሰባት አባላት ያሉት ቦርድ በፆታ ስብጥር 43% ሴቶች ሲሆኑ በመደበኛ በየሩብ ዓመቱ እየተገናኘ የፕሮግራም፤ የፋይናንስ አፈፃፀም፤ የአመራርና ስትራቴጂክ ጉዳዮችን ይመረምራል፤ ያፀድቃል ፤ አዳዲስ ስልቶችን እና ምክረ ሃሳቦችን ይሰጣል፤ ልዩ ልዩ መመሪያዎችን ያፀድቃል። በተጨማሪም የመደበኛ ጊዜውን ሳይጠብቅ አስቸኳይ ስብሰባዎችን እያካሄደ ውሳኔዎችን ያሳልፋል። በበጀት ዓመቱ የድርጅቱ መዋቅር ማሻሻያ፤ የሰው ኃብት አስተዳደር መመሪያ የመሳሰሉት በቦርዱ ፀድቀው ተግባራዊ ሆነዋል።

የዋና ዋና ስራ ክፍሎች ኃላፊዎችን በአባልነት የያዘው እና በዋና ስራ አስኪያጅ ሰብሳቢነት የሚመራው የድርጅቱ ስራ አመራር በበኩሉ በየጊዜው እየተገናኘ የእለት ተእለት ስራዎችን ሂደት እና አፈፃፀም የመምራትና የመከታተል ተግባራትን አከናውኗል።

## 4. የፋይናንስ አፈፃፀም

### 4.1 የገቢ ትንተና

#### 4.1.1 የ2013/2014 በጀት ዓመት የገቢ አፈፃፀም

በበጀት ዓመቱ ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ በሀብት አሰባሰብ ከእቅድ በላይ ማከናወን ችሏል። የተገኘው ገቢ ከለጋሽ ድርጅቶች፤ ከሀገር ውስጥ በመንግስት-የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አጋርነት ፕሮግራምና የገቢ ማስገኛ ስራዎች የተሰባሰበ ሲሆን የሀገር ውስጥ የገቢ አፈፃፀም ከእቅድ አንፃር ዝቅ ያለበት ምክንያት በዓመቱ ከነበረው የአለመረጋጋት እና የሰላም ችግሮች ጋር የሚያያዝ ነው። ከመንግስት ማህበረሰብ -የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አጋርነት የተገኘው ገቢ ከስፖንሰርሽፕ፤ ከልገሳ እና ከአባልነት ነው። በአጠቃላይ የድርጅቱ ዓመታዊ በጀት ከዓመት ወደ ዓመት እያደገ ነው። ለአብነት የ2013/14 ዓ.ም የገቢ አፈፃፀም ከ2012/13 ዓ.ም በ19% ጨምሯል።

| የገቢ ምንጭ | ዕቅድ | ክንውን | ክንውን በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| ለጋሽ ድርጅቶች | 45,095,418.88 | 64,537,166.81 | 143% |
| የመንግስት- የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አጋርነት | 29,779,993.60 | 21,884,354.09 | 73% |
| የገቢ ማስገኛ ተግባራት (ክሊኒኮች እና ሌሎችም) | 10,210,283.52 | 4,926,915.23 | 48% |
| ድምር | 85,085,696.00 | 91,348,436.13 | 107% |
| ከአለፈው ዓመት የዞረ | | 20,114,473.33 | |
| ለዓመቱ የነበረ ጠቅላላ በጀት | | 111,462,909.46 | |


## 4.2 የወጪ ዝርዝር

ለበጀት ዓመቱ የነበረ ጠቅላላ በጀት 111,462,909.46 ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ስራ ላይ የዋለው 87,861,993.88 ብር (79%) ነው። ከዚህ በታች የተመለከተው ግራፍ የበጀት አፈፃፀም ንፅፅር ያሳያል።

በሌላ በኩል ለዓመቱ ከተቀመጠው የበጀት እቅድ በተጣጣመ ሁኔታ ለፕሮግራም ማስፈፀሚያ የወጣው ወጪ 86% ሲሆን የቀረው 14% ደግሞ ለአስተዳደራዊ ስራዎች ጥቅም ላይ የዋለ ነው።

### የወጪ እቅድ ክንውን አፈፃፀም

| የበጀት አርእስት | እቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| ሀ) የፕሮግራም ስራዎች | 90,504,419.96 | 74,827,661.21 | 83% |
| ለ) የፕሮግራም ማስፈፀሚያ ቁሳቁስ እና መሳሪያዎች | 1,064,757.88 | 1,344,815.67 | 126% |
| ሐ) የሰራተኛ ደመወዝ | 5,323,789.41 | 4,332,617.00 | 81% |
| መ) ስልክ፣ ኢንተርኔት፣ ፖስታ | 1,064,757.88 | 579,373.00 | 54% |
| ሠ) ሌሎች አስተዳደራዊ ወጪዎች | 8,518,063.06 | 6,777,527.00 | 79% |
| **ድምር** | **106,475,788.19** | 87,861,993.88 | **83%** |



# 5. የሰው ኃይል አፈፃፀም

## 5.1 የሰው ኃይል አጠቃቀም

በዚህ ዓመት የድርጅቱ የሰው ኃይል አጠቃቀምን በሚመለከት ድርጅቱ በሚሰራባቸው አካባቢዎች በአጠቃላይ 130 ቋሚ ባለሙያና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች የፕሮጀክት ስራዎችን ሲያከናውኑ የቆዩ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 44.6% ሴቶች ናቸው፡፡ ዝርዝሩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

በሪፖርት ዘመኑ በድርጅቱ ውስጥ ስራ ላይ የነበሩ የሰው ኃይል በፆታ እና በትምህርት ደረጃ

| ተ.ቁ. | የትምህርት ደረጃ | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ኤምኤ/ኤምኤሲሲ | 10 | 1 | 11 |
| 2 | ቢኤ/ቢኤስሲ | 24 | 10 | 34 |
| 3 | ዲፕሎማ | 5 | 12 | 17 |
| 4 | ሰርቲፊኬት | 5 | 10 | 15 |
| 5 | 12ኛ ክፍል እና በታች | 28 | 25 | 53 |
| ድምር | | 72 | 58 | 130 |

## 5.2 የሰራተኞች አቅም ግንባታ አፈፃፀም

በተለያዩ የስራ መደቦች ላይ የሚሰሩ 25 ሰራተኞች የአቅም ግንባታ ስልጠና ወስደዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 18 ባለሙያዎች በሪፖርት አዘገጃጀት፤ አፃፃፍ፤ በፋይናንስ አስተዳደር፤ ክትትል እና ድጋፍ፤ በኤችአይቪ/ኤድስ ዙሪያ፤ በኤክስኤል የመረጃ አያያዝ እና አጠቃቀም ክህሎት ስልጠና ወስደዋል፡፡ በተጨማሪም 7 ሾፌሮች የመኪና አደጋ ተጋላጭነት የመቀነስ እና የደህንነት ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡

# 6. የድርጅቱን ዘላቂነትና የሀብት መሰረት ማጠናከር

## 6.1 የገቢ ማስገኛ (አይጂኤ)

- ድርጅቱን በገቢ ማስገኛ ለማጠናከር በተያዘው እቅድ መሰረት ኢትዮ ፍካት ኃ/የተ/የግ/ማህበር በማቋቋም እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡ የኢትዮ ፍካት ኃ/የተ/የግ/ማህበር የንግድ ፈቃድ ወጥቶለታል: እንዲሁም የባንክ ቼክ ተዘጋጅቶለታል፡፡ በዚህም መሰረት የዳቦ ምርት ለመጀመር ጥረት እየተደረገ ሲሆን በጽ/መሳሪያ ዘርፍ ደግሞ በአነስተኛ ደረጃ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡
- በሃዋሳ ከተማ ድርጅቱ የጽ/መሳሪያና የአልባሳት ንግድ ፈቃድ የወሰደ ሲሆን የባንክ አካውንት በመክፈትና ተወካይ በመመደብ እየሰራ ይገኛል፡፡

# 7. ክትትል እና ድጋፍ፤ መረጃ አደረጃጀት

የክትትልና ድጋፍ የስራ ክፍል በየጊዜው የፕሮጀክቶችን እቅድና አፈፃፀም፡ የበጀት አጠቃቀም፤ ጥንካሬዎችን ድክመቶችን እየለየ ለማኔጅመንት ያቀርባል፤ ያስወስናል፡፡ ሪፖርት ያዘጋጃል ለሚመለከታቸው እንዲቀርቡ ያደርጋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በበጀት ዓመቱ ከተከናወኑት ስራዎች የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- የፈፃሚ ድርጅቶች የዳታ ቤዝ ባለሙያዎች መሰረታዊ የ3 ቀን የመረጃ አሰባሰብና ወደ መረጃ ቋት የማስገባት የሙያ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡
- ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተውጣጣ በፕሮጀክቱ የሚሰጡ አገልግሎቶችንና የመረጃ ጥራትን የሚያሻሽል ቡድን በደቡብና ሲዳማ በሚፈፀምባቸው 10 ከተሞች እንዲቋቋም ተደርጎ አበረታች ስራ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ኮሚቴው በየወሩ እየተሰባሰበ ስራውን ይገመግማል ለችግሮች መፍትሄ ያፈላልጋል፡፡




*የጥራት ማሻሻያ ኮሚቴ ወርሃዊ ውይይት በሃዋሳ*

- ድርጅቱ በሚሰራባቸው ከተሞች ከ4 ጊዜ በላይ የፕሮጀክቶችን አፈፃፀም በሚመለከት ድጋፋዊ ክትትል ተደርጓል።
- የጥራት ማሻሻል አማካሪ ባለሙያ በተወሰኑ ከተሞች ድጋፋዊ ክትትል በማድረግ የጥራት ማሻሻል ኮሚቴዎች እንዲጠናከሩ ሙያዊ እገዛ አድርገዋል።
- የደቡብ ክልል ጤና ቢሮ የሚያስተባብረው እና ሁሉም ዞኖች፣ የጤና ተቋማት ባለሙያዎች የሚሳተፉበት በየሁለት ሳምንቱ የሚካሄድ በኤችአይቪ ኤድስ ላይ የሚከናወኑ ተግባራት የሚገመገሙበት ስብሰባ ላይ መሳተፍ ተችሏል።
- ለፕሮጀክቱ ስራ ማስፈፀሚያ የሚሆኑ የክትትልና ድጋፍ፣ የሪፖርት ቅፆች፣ መመሪያዎች የማሰራጨት ስራ ተከናውኗል።
- የለጋሽ ድርጅቶች እና የመንግስት ሪፖርቶች በወቅቱ እንዲላኩ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ፡ እንዳስፈላጊነቱ በማጠናቀር ሪፖርቱ በወቅቱ እንዲላክ ጥረት ተደርጓል

# 8. ሌሎች ዋና ዋና ክንውኖች

## 8.1 የድርጅቱ መዋቅራዊ ማሻሻያ እና የአሰራር ስርዓትን ማጠናከር

- በውጭ አማካሪ ድርጅት በተከናወነው የድርጅቱ የመዋቅር ማሻሻያ ጥናት መሰረት የተግባራት እቅድ እቅድ በማዘጋጀት ማከናወን ተችሏል።
- የድርጅቱ ስትራቴጂክ እቅድ ከወቅታዊ ሁኔታዎች አንፃር እንዲሻሻል ተደርጓል
- የድርጅቱ የአሰራር ስርዓት ለማሻሻል የሚያስችሉ የፈንድ አስተዳደር መመሪያ፣ የሰው ኃይል አስተዳደር ፖሊሲ፣ የሰራተኛ ዓመታዊ ፈቃድ አሰጣጥ ፖሊሲ ተዘጋጅተዋል። ሌሎችን የማሟላት ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛል።

## 9 የ2014/2015 ዓመት በጀት እቅድ

ድርጅቱ የ2013/14 በጀት ዓመት አፈፃፀም የነበሩትን ጥንካሬዎች እና ጉድለቶች በመፈተሽ ፤ ውስጣዊና ውጫዊ ምቹ ሁኔታዎችን እና ተፅእኖዎችን በመገምገም፤ ሁሉንም የስራ ክፍሎች በሂደቱ በሚገባ እንዲሳተፉበት በማድረግ አዳዲስ የማስፈፀሚያ ስልቶችን በመቀመር የ2014/15 እቅድ አዘጋጅቷል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ለማዕከላቱ ግንባታ የሚያስፈልገውን ገንዘብ የማሰባሰብ ስራ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት አበረታች ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን በ2014/15 የበጀት ዓመት እና ከዚያም በኋላ ባሉት ጊዜያት ለማሳካት የተለያዩ የማህበረሰብ ንቅናቄ እና የሀብት አሰባሰብ ስራዎች ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚተገበሩ ይሆናል፡፡

በዚህም መሰረት የትምህርት፤ ጤና፤ የኢኮኖሚ አቅም ግንባታ፤ ተቋማዊ አቅም ግንባታ እንዲሁም ስነ-ተዋልዶ ጤና፤ ስርዓተ-ፆታ ልማት እና ኤችአይቢ/ኤድስን ስራዎች ለማከናወን 107,747,222 ብር ታቅዷል፡፡ በአጠቃላይ ከ200 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያስፈልጋቸው የማዕከላት እና የሁለገብ አገልግሎት መስጫ ህንፃ ግንባታ ፕሮጀክቶች ከበጀት ዓመቱ ዋና ዋና ተግባራት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ የልማት ስራዎቹም ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ያካትታል፡-

- የጤና መከላክልና ህክምና አገልግሎት ስራዎች
- የትምህርት ተደራሽነትና ጥራት ማሻሻያ ተግባራት
- የኑሮ ማሻሻያ እና የድህነት ቅነሳ ስራዎች
- የስነ-ተዋልዶ ጤና፤ ፆታ- ተኮር ጥቃት መከላከል፤ የሴቶች እና ህፃናት አቅም ግንባታ
- የተቀናጀ የማህበራዊ አገልግሎት ስራዎች
- የማዕከላት እና ሁለገብ አገልግሎት መስጫ ህንፃዎች ግንባታ
- የድርጅቱን የልማት ስራዎች ወደ ሌሎች ክልሎች እና ከተሞች ማስፋት ለምሳሌ ሀረር፤ ጂማ፤ በአማራ ክልል ሸዋ ሮቢት እና አጣዬ
- የተቋም አቅም ግንባታ እና የአሰራር ስርዓትን ማጠናከር፡፡

የዋና ዋና ስራዎች እና በጀት እቅድ ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል

| ተ.ቁ. | ተግባራት | በጀት | |
|---|---|---|---|
| **የፕሮግራም ስራዎች** | | | |
| **1** | **ጤና** | | |
| ውጤት1፤ ድርጅቱ በሚሰራባቸው አካባቢዎች የ100,000 የማህበረሰብ አባላትን የጤና ግንዛቤ እና ተጠቃሚነት ማሳደግ | | | |
| | በሳንባ ካንሰር፤ ኤችአይቪ/ኤድስ መከላከል፤ ድጋፍ እና ህክምና ዙሪያ በግንዛቤ መስጫ መልእክቶች እና ስልጠና የጤና ባለሙያዎችን እና የማህበረሰቡን አቅም መገንባት | 3,861,740.00 | |
| | ለማህበረሰቡ የጤና ትምህርቶችን ተደራሽ ማድረግ | 110,000.00 | |
| ውጤት2፤ የተቀናጀ የጤና አገልግሎት ለ48,000 የህብረተሰብ ክፍሎት ተደራሽ ማድረግ | | | |
| | በማህበረሰብ ውይይት፤ በማህበራዊ ሚዲያ፤ መገናኛ ብዙሃን፤ በድራማ እና መዝሙር ክለቦች በስነ ተዋልዶ | 21,960.00 | |

| ተ.ቁ. | ተግባራት | በጀት | |
|---|---|---|---|
| | ጤና፣ ፆታ ተኮር ጥቃት መከላከል ላይ ትምህርት መስጠት | | |
| | የማህበረሰብ ጥምረት ቡድኖችን ማጠናከር፣ ማህበረሰብ አቀፍ የፀረ-ኤችአይቪ መድሃኒት እና የህክምና አገልግሎቶችን ማጠናከር | 12,787,499.00 | |
| | በጤና ተቋማት የህክምና፣ የእናቶች እና ህፃናት፣ የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር፣ ቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትን መስጠት | 3,006,200.00 | |
| 2 | **የኢኮኖሚ አቅም ግንባታ እና ኑሮ ማሻሻያ** | | |
| ውጤት1፤ የ5000 የህብረተሰብ ክፍሎችን ድህነት መቀነስ፤ ኑሯቸውን ማሻሻል | | | |
| | የህፃናት ስፖንሰርሺፕ ድጋፍ መስጠት | 10,547,600.00 | |
| | የአረጋዊያን ስፖንሰርሺፕ ድጋፍ መስጠት | 1,758,400.00 | |
| | ማህበረሰብ-አቀፍ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ ለህፃናት መስጠት | 3,344,000.00 | |
| | የሃዋሳ አረጋዊያን ማዕከሉን አገልግሎት ማጠናክር | 2,309,200.00 | |
| | የሆሳዕና እና አርባ ምንጭ ማዕከላት፣ የአዲስ አበባ ህንፃ ግንባታ ማካሄድ | 14,000,000.00 | |
| | ሴቶችን፣ የህፃናት አሳዳጊዎችን በራስ አገዝ፣ የቁጠባ እና ብድር ቡድን ስልጠና መስጠት ፣ ማደራጀት | 2,363,000.00 | |
| | ለወጣቶች እና ታዳጊ ወጣቶች የኢኮኖሚ አቅም ግንባታ ድጋፍ ማድረግ | 6,588,040.00 | |
| 3 | **ትምህርት አገልግሎት** | | |
| ውጤት1፤ እድሜያቸው ለትምህርት ለደረሱ 9,000 ተማሪዎች የትምህርት ተደራሽነት ማሻሻያ እና ጥራት ዚሪያ ድጋፍ መስጠት | | | |
| | ለህፃናት እና ወጣቶች የቤተ-መፃህፍት፣ የኮምፒዩተር፣ የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ፣ ነፃ የትምህርት እድል መስጠት፣ ማመቻቸት | 507,362.00 | |
| | የት/ቤት አቅም ግንባታ (መሰረተ ልማትን የአሰራር ስርዓትን ማጠናከር) | 550,000.00 | |
| | የድጋፋዊ ክትትልን ከመንግስት እና ማህበረሰቡ ጋር በመተባበር በየሩ/ዓመቱ ማካሄድ | 1,868,119.00 | |
| 4 | **ተቋማዊ አቅም ግንባታ** | | |
| ውጤት 1፡ የድርጅቱን ሀብት የማሰባሰብ አቅም አሁን ካለበት በ58% ማሳደግ | | | |
| | የተለያዩ የሃብት ማሰባሰብ የቅስቀሳ ፅሁፎችን፣ ማህበራዊ ሚዲያ፣ ማስ ሚዲያ መጠቀም እና ኩነቶችን ማካሄድ | 317,000.00 | |
| | የሃብት ማሰባሰብ የስራ ክፍል በዋናው ቢሮ ማደራጀት፣ በሰው ኃይል ማጠናከር | 750,000.00 | |
| ውጤት 2፡ የድርጅቱን ተደራሽነት ከ5 ወደ 7 ክልሎች ማሳደግ | | | |

| ተ.ቁ. | ተግባራት | በጀት | |
|---|---|---|---|
| | ፕሮግራሞቹን በኦሮሚያ በጂማ፤ በሀረር እና በአማራ ክልል በሸዋ ሮቢት እና አጣዬ ማስፋት | 180,000.00 | |
| ውጤት 3፡ የዲያስፖራ ማህበረሰብን ተሳትፎ እና አጋርነት ማጠናከር | | | |
| | ከኢትዮጵያ ዲያስፖራ ኤጀንሲ ጋር የእቅድ ዝግጅት ውይይቶችን ማከናወን | 65,000.00 | |
| | የዲያስፖራ ንቅናቄ ስራዎችን ማከናወን | 70,000.00 | |
| | በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር በሚካሄዱ የዲያስፖራ ማህበረሰብ ልዩ ልዩ ስብሰባዎች እና ኩነቶች ላይ መሳተፍ | 350,000.00 | |
| ውጤት 4፡ የሰራተኛውን እውቀት እና ክህሎት በማሳደግ የተሻለ የፕሮጀክት አፈፃፀም እና የፕሮግራም ዘላቂነትን ማረጋገጥ | | | |
| | ሰራተኛውን በስልጠና እና ትምህርት ማብቃት | 230,000.00 | |
| | የፕሮግራም ሰራተኞች ደመወዝ | 24,575,521.00 | |
| | የፕሮግራም በጀት - ድምር | 90,160,641.00 | |
| አስተዳደራዊ ወጪዎች | | | |
| | የቢሮ ቁሳቁስ፤ መሳሪያዎች እና ሌሎች አስተዳደራዊ ወጪዎች | 8,045,851.28 | |
| | የአስተዳደር ሰራተኞች ደመወዝ | 9,540,730.00 | |
| | የአስተዳደራዊ ስራዎች በጀት - ድምር | 17,586,581.28 | |
| | ጠቅላላ በጀት | 107,747,222.28 | |

- ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ይህን ሃብት የሚያሰባስበው ከለጋሽ ድርጅቶች 57%፡ ከመንግስት-የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አጋርነት 37% እና ከገቢ ማስገኛ ስራዎች 6% ይሆናል፡፡ ለፕሮግራም ስራዎች 90,160,641 ብር (84%) እንዲሁም ለአስተዳደራዊ ስራዎች ማስፈፀሚያ 17,586,581 ብር (16%) ተመድቧል፡፡

- የታቀዱትን የፕሮጀክት ተግባራት እና በጀት እንደተለመደው ከመንግስታዊ ቢሮዎችና መዋቅር፡ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፤ ከሴቶች፡ ህፃናትና ወጣቶች አደረጃጀቶች፡ ከንግዱ ማህበረሰብና ከህብረተሰቡ፡ ከኪነ ጥበብ እና መገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች፤ ከዲያስፖራው ማህበረሰብ ጋር በመተባበር የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

## 10. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች

### 10.1 ያጋጠሙ ችግሮች

- በበጀት ዓመቱ በሀገሪቱ በተቀሰቀሰው ጦርነት፤ የሰላም መደፍረስና አለመረጋጋት የሀገር ወስጥ የማህበረሰብ ንቅናቄ እና ሀብት ማሰባሰብ ስራችን ላይ ተፅእኖ አሳድሯል

- ድርጅቱ በሚሰራባቸው አንዳንድ አካባቢዎች በፈንድ እጥረት የማህበረሰቡን ችግሮች እና ፍላጎቶች አጥጋቢ በሆነ መንገድ መፍታት ያልተቻለበት ሁኔታ ነበር

## 10.2 መፍትሄዎች

- እቅዶቻችንን በመከለስ እና ሚዲያን በመጠቀም ህብረተሰቡን ለመድረስ ጥረት ተደርጓል
- ተጨማሪ ፕሮጀክቶችን በማምጣት እና የሃብት ማሰባሰብ ስልቶችን በመከለስ የድርጅቱን ገቢ ማሳደግ፤ተጠቃሚዎችን በተሻለ ሁኔታ ተደራሽ ማድረግ

# 11. ምስጋና

ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ከዚህ በታች ለተጠቀሱት ለጋሽ ድርጅቶች፤ ደጋፊዎች እና ሁሉንም መዘርዘር ስለማይቻል ሌሎች ያልተጠቀሱትን ከፍተኛ ምስጋና እና አክብሮቱን ይገልፃል፡

- ዩኤስኤይድ /የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ትብብር ድርጅት/
- ዓለም አቀፍ የፍልሰተኞች ድርጅት
- ዓለም አቀፍ ስነ-ህዝብ ፈንድ /ዩኤንኤፍፒኤ/
- ዓለም ባንክ
- ስቲሊ አርኤምአይ ኃ/የተ/የግ/ ድርጅት
- ኖህ ሪል እስቴት ኃ/የተ/የግ/ድርጅት
- የግል ባለሃብቱና በጎ አድራጊ ግለሰቦች
- መንግስት

እንዲሁም በቴክኒክ፤ ሙያ እገዛ፤ በአቅም ግንባታ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላደረጉ፤

- • ፕሮጀክት ሆፕ
- • ኤፍኤችአይ 360
- • አሳፕ / ኢንትራ ሄልዝ ኢንተርናሽናል

# 12. የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት

## 13. አባሪ

# የስኬት ታሪኮች

### 1. ታሪኬ ተቀይሯል



ስም፡ ወ/ሮ አበበች እጅጉ
አድራሻ፡ አዲስ አበባ የካ ወረዳ 02
ዕድሜ፡-50

“ከዛሬ 23 ዓመታት በፊት ጊዜው የኤች አይ ቪ ኤድስ ወረርሽኝ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ቀውስ ያደረሰበትና በርካቶችን ለሞት የዳረገበት ነበር፡፡ እኔም በኤችአይቪ ተይዤ የነበረበት ወቅት ነበር” ትላለች ባለታሪክ አበበች፡፡ “ቫይረሱ የነበረባቸው ሰዎች በግንዛቤ ችግር እና ስለህመሙ በነበረው የተዛባ አመለካከት ቤተሰብን ጨምሮ በማህበረሰቡ ከፍተኛ መገለል ይደርስ ነበር፤ እኔም የዚሁ ሰለባ ነበርኩ፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ወደ ሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ የድጋፍ ፕሮግራም እንድገባ እድሉ ተፈጥሮልኝ፤ በተሰጠኝ ምክር አገልግሎት፤ ክትትልና ድጋፍ ጠንካራ ስነልቦና እና በራስ መተማመን እንዲኖረኝ የረዳኝ ሲሆን በወር 660 ብር ከሚሰጠኝ እየቆጠብኩ በአሁን ሰዓት እንጀራ በመጋገር እና በመሸጥ፣ ጉልት በመቸርቸር እና የተለያዩ ስፌቶችን በመስራት እኔንም ቤተሰቤንም እያስተዳደርኩ እገኛለሁ፡፡ ታሪኬ ተቀይሯል፡፡ ሰዎች ከኤች አይ ቪ ኤድስ እና ከሌሎች በሽታዎች እንዲጠበቁ እያስተማርኩ እገኛለሁ፡፡” በማለት ህይወቷ መለወጡን፤ በጥረቷ የነገው ኑሮዋ የተሻለ እንደሚሆን ትልቅ ተስፋ እንደሰነቀች ገልፃለች፡፡

### 2. የነገን ህይወት ብሩህ የሚያደርገው እውቀት ነው





ስም ናትናኤል ዳዊት
ፆታ ወንድ
ዕድሜ 23
አድራሻ አዲስ ከተማ ሃዋሳ

ናትናኤል በሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ሃዋሳ የወጣቶችና ህጻናት ማዕከል ተጠቃሚ የሆነው ገና በህፃንነቱ ነበር፡፡ የንባብ ልምዱን ያዳበረው በህፃናት ቤተ መፀሃፍት ክፍል ነበር፡፡ ቀስ በቀስ እድሜውም እያደገ ሲመጣ ወደ ወጣቶች ቤተመፃህፍት ክፍል ተዛወረ፡፡ ናትናኤል ለአስራ አንድ ዓመታት በቤተመፃህፍቱ አገልግሎት የተጠቀመ ሲሆን ይህም የንባብ ልምዱንና ፍላጎቱን ወደ ከፍተኛ ደረጃ አሳድጎለታል፡፡ በመሆኑም ናትናኤል ስሜቱን እንዲህ ሲል ይገልፃል “አሁን ላለሁበት ደረጃ እንድበቃ የሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ቤተ መፃህፍት ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቶልኛል፡፡ በአሁኑ ወቅት ወጣትነት ዕድሜ ላይ ስሆን ይህንንም በአግባቡ መጠቀም በመቻሌ ለከፍተኛ የትምህርት ተቋም በቅቻለሁ፤ በሃዋሳ ዩኒቨርሲቲም የ3ኛ ዓመት ትምህርቴን በመከታተል ላይ እገኛለሁ፡፡ እንደ እግዚአብሄር ፍቃድ ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ በህክምና ዶክትሬት ዲግሪ እመረቃለሁ፡፡ የሜሪ ጆይ ኢትዮጵያ ህፃናትና ወጣቶች ማዕከል በህይወቴ ትልቅ ለውጥ እንዲኖረኝ[1] ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጎልኛል ከልብ አመሰግናችኋለሁ፡፡” በማለት ለህይወቱ መለወጥ ማዕከሉ የነበረውን አስተዋፅኦ ገልፆታል፡፡

## ትምህርት



የትምህርት ማጣቀሻ ድጋፍ

## ጤና



ሳንባ ካንሰር ትምህርት



አዲስ አበባ ህክምና ማዕከል





# የኢኮኖሚ አቅም ግንባታ / ገቢ ማስገኛ




በፕሮጀክት ድጋፍ በገቢ ማስገኛ ስራ የተሰማሩ ሴቶች እና ወጣቶች



የሳንባ ካንሰር ስልጠና እና ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች

# የመንግስት - ማህበረሰብ - የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ አጋርነት



አርቲስት መቅደስ ፀጋዬ 10 ህፃናት ስፖንሰር አድርገዋል






የበዓላት የዓይነት ድጋፍ



የአልባሳት ድጋፍ



የምገባ ፕሮግራም





ሃዋሳ አረጋዊያን ማዕከል



በጎ ፈቃደኞች በአዲስ አበባ



ለአረጋዊያን ማዕከላት ግንባታ የማህበረሰብ ንቅናቄ በአርባምንጭ